# ለሂዩማን ራይትስ ዎች የተሰጠ ምላሽ

**(ክፍል - አንድ)**

በገነነው አሰፋ
(ትርጉም በእስኬው ዚ.)

እንደ ሂዩማን ራይትስ ያሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶችን እየጣሰ ነው በማለት ተጨባጭነት የሌላቸውን ክሶች በመደርደር በሀገራችን ላይ የሚያካሂዱትን ማቆሚያ የሌለው ውንጀላ ያቆሙበት ጊዜ መኖሩ እስከ ዛሬ አልታየም።

ከድህነት ለመላቀቅና ብልፅግናን ለማምጣት በፈጣን የለውጥ ሂደት ውስጥ ያለችው አገራችን ዓለም አድናቆት የቸረው የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበች ነው። ይህ ማለት ግን በምታካሂደው የለውጥ ሂደት የተለያዩ ጉድለቶችና ውስንነቶች የሉባትም ማለት አይደለም፤ አሉባት። ይሁን እንጂ የተለያዩ ጉድለቶችና ውስንነቶች ቢያጋጥማትም የዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የሚያስችል ፅኑ መሰረት ጥላለች፤ በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እያበበ ካለባቸው አገሮችም በቀዳሚነት ተጠቃሽ ለመሆን በቅታለች። ወደፊትም በብሄር/ብሄረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ የአንድነት መርኋን አጠናካራ እስከተገበረች ድረስ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ቀዳሚውን ስፍራ እንደያዘች መቀጠሏ አጠያያቂ አይደለም። ለዚህም ነው ላለፉት 23 ዓመታት የምትመራበት ፌዴራላዊ የመንግስት አወቃቀር ስርዓት አገሪቷን መበታተኑ አይቀርም ተብሎ ብዙ ቢነገርም ከመነገር ያለፈ ፋይዳ ግን ሊኖረው አልቻለም፤ በአንፃሩ ሀገራችን በአፍሪካ የሰላምና መረጋጋት ተምሳሌት ለመሆን የበቃች አገር ሆናለች። በዚህም ሳቢያ አገራችን በዓለማችን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገቡ ካሉ ጥቂት አገራት አንዷ በመሆን የመካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ በምታደርገው ግስጋሴ በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ለመሆን የበቃችው።

አገራችን በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ፌዴራላዊ የመንግስት ስርዓት የምትመራ ከመሆኗ አኳያ በየትኛውም ዓለም አቀፍ መመዘኛ የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የምታራምድ አገር ነች። ለዚህም የበርካታ ብሄር/ብሄረሰቦች አገር መሆኗን (የሀገሪቱን

ብዝሃነትን) በሚያንፀባርቅ መልኩ በሕዝብ በተመረጠ አራት የተለያዩ ብሄረሰብ ፓርቲዎች ግንባር ፈጥረው በመሰረቱት ጠንካራ መንግስት የምትመራ መሆኗን በማሳያነት መጥቀሱ ብቻ ይበቃል።

የግንባሩ አባል የሆኑት ፓርቲዎች በፌዴራላዊ ሕገ መንግስት ለተደነገጉት የሰብዓዊ መብት ህግጋቶች መከበር ፅኑ እምነት ያላቸው በመሆኑ በአፈፃፀም ረገድ የሚሰነዘሩ ሂሶችን በመቀበልና በችግሮቹ ላይ በግልፅ በመወያየት የተለያዩ የማሻሻያ እርምጃዎች ከመውሰድ ተቆጥበው አያውቁም። በዚሁ መሰረት የሀገራችን ከፍተኛ ፖሊሲ አውጭዎች ቡድን እ.ኤ.አ. በ2013 ዓ.ም የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ ያወጣውን ሪፖርት በጥልቀት ከመረመረና ከተወያየ በኋላ ባወጣው መግለጫ የአሜሪካኑ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ያወጣው ይህ ሪፖርት ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ላይ ካቀረበው ሪፖርት የረባ ልዩነት እንኳን አለማየቱን ነው የገለፀው።

የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ይህን ሪፖርት ያወጣው የሰብዓዊ መብት አያያዝን በተመለከተ ያካሄደውን ዓለም አቀፍ ጥናት መሰረት በማድረግ እንደሆነ ነው የገለፀው። የኢህአዴግ መንግስት ግን በሪፖርቱ ላይ በአዲስ መልክ ከቀረቡትና እዚህ ግቡ የማይባሉ ውንጀላዎች በስተቀር በአብዛኛው ቀደም ሲል ተሰንዝረው የነበሩት ክሶች ተገልብጠው እንደገና መቅረባቸውን ነው ከሪፖርቱ መረዳት የቻለው።

በ2013 የወጣውን የድርጅቱን ሪፖርት ይዘት ስንመለከት ለራሱ ጥቅምና ፍላጎት የቆሙ፣ የተመረጡ የፖለቲካ ተቃዋሚ ኃይሎችን በመረጃ ምንጭነት/አስረጅነት የተጠቀመ ሆኖ ነው የምናገኘው። ሪፖርቱ የዓይን እማኞችን ምስክርነት መሰረት ያደረገ መሆኑን፣ ነገር ግን ለእነዚህ የዓይን እማኞች ሕይወት ደህንነት ሲባል ስማቸው አለመጠቀሱን ይገልፃል። እነዚህን የዓይን እማኞች በአስረጅነት በመጥቀስ የቀረቡት የሰብዓዊ መብት ውንጀላዎች ከእውነታው ጋር ቅንጣት ተዛማጅነት የሌላቸው መሆኑ ለማንም ግልፅ ሆኖ እያለ ነው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ስማቸው ያልተጠቀሱ እማኞች የሰጡት መረጃ ተአማኒ (እውነተኛ) ለመሆን ኃላፊነቱን እንደሚወስድ የተናገረው።

አይደለም ዓለም በሰለጠነበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን ቀርቶ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን እንኳን የከሳሽን ማንነት ከተከሳሹ በመደበቅ መወንጀል እና ያቀረብኩት ውንጀላ እውነተኛ መሆኑን እመኑኝ ማለት ተቀባይነት አልነበረውም።

በማንኛውም ወቅት ይህን ምስክርነት የሰጡት የዓይን እማኞች እውነተኛ ማንነታቸውንና ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳቸው የተሸፈነ ቢመስልም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ባወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ላይ የሰፈሩትን ክሶች ድምፀት እና ቋንቋ ለተመለከተ፣ እነዚህ ስም-አልባ እማኞች በሀገራቸው ያለው ህጋዊ ስርዓት ዓላማቸውን ለማራመድ አልመቻቸው ሲል ወደ ውጭ ሀገር ተሰደው በሀገር ውስጥ አልሳካ ያላቸውን ድብቅ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ኃይሎች መሆናቸውን ለመገንዘብ አያዳግትም። እነዚህ ወይም አሁን ያለውን መንግስት በአመፅና በሁከት የማፍረስ ፅኑ ፍላጎት ያላቸው እነዚህ ኃይሎች ራሳቸውን የተካኑ መሆናቸው የታወቀ ነው።

ስለዚህ እነዚህ ሀይሎች የኢትዮጵያን መንግስት በሀሰት ለመወንጀል ሌት ተቀን ቢራወጡ ምንም የሚያስገርም ነገር ሊኖር አይችልም። የሚያስገርመው ይህንን ፀሀይ የሞቀው እውነታ ከዓለም ለመደበቅ የሚያደርጉት ከንቱ ሩጫ ነው።

እነዚህ የፖለቲካ ጀብደኞች በሚያራምዱት የፖለቲካ ዓላማ ሳቢያ ተጠያቂ በማይሆኑበት አገር ተቀምጠው ማንኛውንም ዘዴ (አማራጭ) ተጠቅመው ህጋዊውን የኢትዮጵያ መንግስት ከስልጣን ለማውረድ የጀመሩትን ጥረት እንደሚገፉበት በአደባባይ ቃል ገብተዋል። ነገር ግን ዓይናችንን ገልጠን ስንመለከተው የዋሁን የህብረተሰብ ክፍል በቀላሉ ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚመሩት እነዚህ የበግ ለምድ ለባሾች ናቸው በአሜሪካ ኮንግረስ *ከወገንተኝነት የፀዳ ምስክርነት* የሰጡ ወገኖች ተደርገው የቀረቡልን።

እነዚህ የበግ ለምድ ለባሾች በአሜሪካን ህግ አውጪ ፓርላማ ተጠርተው ምስክርነታቸውን መስጠታቸው በሪፖርቱ ተገልጿል። ነገር ግን እነዚህ ኃይሎች በአሜሪካ ኮንግረስ ሕግ አውጪዎች ፊት ቀርበው የሰጡት ምስክርነት እውነት ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል።

ይህ እንዳለ ሆኖ እነዚህ ኃይሎች በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት በኢትዮጵያ ላይ ባወጣው ሪፖርት ላይ በአሜሪካ ኮንግረስ ንዑስ ኮሚቴዎች ፊት ቀርበው ቃላቸውን ከሰጡ የምስክሮች ስም ዝርዝር ውስጥ እውነተኛ ስማቸው ተጠቅሶ ይገኛል። ለአሜሪካ ውጭ

ጉዳይ መ/ቤት ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እውነተኛ ስማቸውን መደበቅ የመረጡት እነዚህ ኃይሎች በአሜሪካ ኮንግረስ ንዑስ ኮሚቴዎች ፊት ቀርበው የአዞ እንባቸውን እያነቡ የሀሰት ውንጀላዎችን ሲደረድሩ ግን እውነተኛ ማንነታቸውን በሚደብቅ የሀሰት ስም መጠራት አላስፈላጋቸውም። ግንባር ቀደም እማኞቹ በአሜሪካ ህግ አውጭ አካል ፊት ቀርበው ምስክርነታቸውን ሲሰጡ የፖለቲካ ዓላማቸውን ሁከትና አመፅ በመቀስቀስ የማሳካት ዓላማ እንዳላቸው በግልፅ ለመናገር አልደፈሩም። እነዚህ እንደየሁኔታው መልካቸውን የሚቀያይሩት እስስቶች በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው በሚያካሂዱት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ ግን እውነተኛ ማንነታቸውን ለማሳየት ፍርሃት አላደረባቸውም፤ በሌላ አባባል ወገኖች እነዚህ እስስቶች ለኮንግረንሱ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እውነተኛ ዓላማ'ቸውን ቢደብቁም በፈንድ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ላይ ግን በኢህአዴግ መንግስት ላይ የትጥቅ ትግል ለመሰንዘር ማቀዳቸውን በአደባባይ ሲለፍፉ ምንም አይነት ፍርሃት አላደረባቸውም። የ1997ን አገራዊ ምርጫ ተከትሎ ከተፈጠረው ቀውስ ጋር በማያያዝ "በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ጠቧል" የሚለውን የተቃዋሚዎች የተለመደ ጩኸት እንደገና በማስተጋባት እርስ በርሱ የሚጋጭ አቋማቸውን ለማስታረቅ ሲሞክሩ ተስተውለዋል። እዚህ ላይ እጅግ አሳዛኙና ልብ ሊባል የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ እነዚህ አቋም የለሽ ፀረዲሞክራሲ ሀይሎች *የ1997 ምርጫ በሀሰት ተጨበርብሯል* በማለት የጎዳና ላይ ነውጥ ከቀሰቀሱ በኋላ ነውጡ ላስከተለው አደጋ ኃላፊነት ለመውሰድ የሚያስችል የሞራል ጥንካሬ ያልነበራቸው መሆኑ ነው። ይህም በአንድ በኩል ቆመንለታል ለሚሉት ዓላማ መስዋዕትነት ለመክፈል እንደማይፈልጉና በዚህም ሳቢያ ሕዝቡን ለድብቅ ዓላማቸው ማስፈፀሚያ ማድረጋቸውን ያመለክታል።

እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች ናቸው እንግዲህ ኑሯቸውን በሀገረ አሜሪካ አድርገው በአንድ በኩል "ነፃነት ወይም ሞት!" እያሉ መፈክር ሲያወርዱ በሌላ በኩል ደግሞ የዓለማችን ሃያል መንግስት ነው ብለው የሚያምኑት የአሜሪካ መንግስት፣ አምባገነን ከሚሉት የኢትዮጳያ መንግስት እንዲጠብቃቸው ሲለምኑ የሚስተዋሉት። መቼ ምን ሊመጣባቸው እንደሚችል ስለማያውቁ ወደ ትውልድ አገራቸው እንዲመለሱ ከተገደዱ የዕድሜ ልክ እስራት እንደሚፈረድባቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ። ራሳቸውን "የነፃነት ታጋዮች ነን"፣ "ለህዝብ ነፃነት ነው የምንታገለው" እንደሚሉት ግን አገራቸው ውስጥ ለአንዲት ቀን እንኳን ውለው ማደር አልቻሉም። "ነፃነት ወይም ሞት" የዘወትር መፈክራቸው ነው፤ ለነፃነት

እስከ ሞት የሚደርስ መስዋዕትነት ለመክፈል ግን ፈቃደኛ አይደሉም። ይህም ቆመንለታል ለሚሉት ዓላማ መስዋዕትነት ከመክፈል ለግል ህይወታቸውና ለደህንነታቸው ቅድሚያ እንደሚሰጡ ያሳያል። ይህም እነሱ ለቆሙለት ዓላማ ሌላውን መስዋዕትነት በማስከፈል እነሱ ኬካቸውን መብላት የመረጡ መሆኑን ያሳያል።

ቃላቸው ከግብራቸው የተለየ መሆኑን የተረዱት እነዚህ የፖለቲካ ሃይሎች ካሉበት አሳፋሪ የሁለት ክፉ ምርጫ (dilemma) ለመውጣት ያላቸው አማራጭ በውጭ አገር የሚቆዩት በኢህአዴግ ላይ ለማካሄድ ያቀዱትን የትጥቅ ትግል አደራጅተው እስከሚጨርሱ እንደሆን አድርገው ማስመሰል ነው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያ ከኢህአዴግ አፋኝ የከፋፍለህ ግዛው አገዛዝ ነፃ መውጣት ካለባት የቀረው ብቸኛው አማራጭ ጫካ መግባት ብቻ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲለፍፉ የሚሰሙት። ይህም ስልታዊ ስትራቴጂያቸው የግል ህይወታቸውን ለምንም ዓይነት አደጋ ሳያጋልጡ ለትጥቅ ትግሉ ማደራጃ በሚል ሰበብ ገንዘብ እንዲያሰባስቡ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል። በአጠቃላይ ከዚህ እውነታ የምንረዳው እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ሃይሎች ወጥ አቋም እንደሌላቸውና በአንዴ ሁለት የተለያየ ዓላማ እንደሚያራምዱ ነው። ለዚህም ተግባራቸው ቀደም ሲል ካነሳነው ማሳያ በተጫማሪ በርካታ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። በዚህ ረገድ በተጨማሪ ማሳያነት ሊቀርብ የሚችለው አንዱ ነጥብ እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ሃይሎች የኢትዮጵያ መንግስት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ፈፅሟል በማለት ለአሜሪካ፣ ለአውሮፓ፣ ለግብፅና ለኤርትራ መንግስታት ምስክርነትና ማብራሪያ መስጠታቸውና ለዚሁ ውለታቸው ዳጎስ ያለ ገንዘብ ከመንግስታቱ መቀበላቸው ነው።

እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች በእነዚህ አገራት እየተዘዋወሩ ይህን ተግባር ከመፈፀም ጎን ለጎን የኢትዮጵያ መንግሥትን ከሥልጣን ለማውረድ መሳሪያ አስታጥቀው ወደ ጫካ የሚያስገቡትን ሃይል ከአሜሪካ ቁጭ ብለው የውጊያ ትዕዛዝ የሚሰጡበት የሳተላይት ቴሌቪዥን አደራጅተዋል። ተቃዋሚ ኃይሎቹ በአንድ በኩል በሀሰት የፈበረኩትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ለሀገራችን ባላንጣ አገራት እውነት አስመስለው በማቅረብ በሌላ በኩል ደግሞ የሀሰት መረጃ ከሚያቀርቡላቸው አገራት በሚያገኙት ገንዘብ የኢሳት ቴሌቪዥን በማደራጀት የኢትዮጵያ መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ ብቸኛው አማራጭ የትጥቅ ትግል መሆኑን በመቀስቀስ ስራ ተጠምደዋል። እነዚህ ኃይሎች በምቾት ለመኖር ሲሉ የሚያካሂዱት ሀሰት በመፈበርክና በማጭበርበር ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እንቅስቃሴ

በሀገረ አሜሪካ ህግ ተጠያቂነት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ይታወቃል። ታዲያ ህጋዊ ተጠያቂነት የሚያስከትልባቸውን ድርጊት ለመፈፀም ጥንካሬውንና ብርታቱን ከየት አገኙ?

በእንደዚህ ዓይነት ህገወጥ ተግባር ላይ ለመሰማራት ያስቻላቸውን ድፍረት ያገኙት በአመዛኙ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት በአሜሪካ ሕግ የተከለከለ ተግባር ሲፈፅሙ እያየ እንዳላየ ሆኖ ማለፍን የመረጠ መሆኑን ስለተረዱ ነው። በአሜሪካ የስደተኞች ህግ ማንኛውም ስደተኛ የትውልድ ሀገሩን መንግስት በኃይል ለመጣል የሚያስችል ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ እንደማይችል የተደነገገ ሆኖ ሳለ የአሜሪካ መንግስት ግን እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች የሀገሪቱን ህግ በሚጥስ ተግባር ላይ መሰማራታቸውን እያየ በዝምታ ማለፉ ገና ያልተፈታ እንቆቅልሽ ነው።

መቼም ሀገራችን በብዙ መስኮች አዎንታዊ ለውጥ እያስመዘገበች መሆኗን የሚያውቅ ማንኛውም ወገን የተቃዋሚ ኃይሎች በኢህአዴግ ላይ ለሚያካሂዱት አሳፋሪ የስም ማጥፋት ተግባር ድጋፍ ይሰጣል ብሎ ለመገመት አዳጋች ከመሆኑም በላይ አስገራሚ ነው።

እዚህ ላይ ለማንሳት የፈለግነው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ከሀገሪቱ ውጭ ባሉ የተለያዩ አገራት ሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ ለሚያወጣው ዓመታዊ ዘገባ በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግሉትን የምርምር ተቋማት ነው። ከወገንተኝነት በፀዳ ጥናት ላይ የተገኙ መረጃዎችን መሰረት ያደረገ ነው የተባለለት ይህ መ/ቤት የኢትዮጵያ መንግስትን ሰብዓዊ መብት አያያዝ አስመልክቶ ያወጣው ዘገባ በግምት ላይ የተመሰረተ፣ በእውነተኛ ማስረጃ ያልተደገፈ እና ከዚህ በፊት ያለ አንዳች ተጨባጭ ማስረጃ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የተሰነዘሩ ተመሳሳይ ውንጀላዎችን ያካተተ መሰረተ ቢስ ክስ ነው።

መ/ቤቱ ላወጣው ለዚህ ዘገባ እውነተኛ መሆን በአስረጅነት የተጠቀሱት ስማቸው ያልተጠቀሰና ማንነታቸው የማይታወቅ ሰዎች ሰጡኝ ያለውን መረጃ ብቻ ሳይሆን ከሀገር ቤት ሸሽተው መኖሪያቸውን በአሜሪካ ያደረጉ አክራሪ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በኢትዮጵያ መንግስት ላይ በተደጋጋሚ የሚሰነዝሩትን ውንጀላዎች ሁሉ ያካተተ ነው። እንግዲህ የአሜሪካ መንግስት እነዚህ ወገኖች የሰጡትን መረጃዎች መሰረት አድርጎ ነው

የኢትዮጵያ መንግስት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እየፈጸመ ነው ሲል ያለ ኃጢአቱ የሚኮንነው። ይህም ብቻ አይደለም ይኸው የሀሰት ውንጀላ የኢትዮጵያ መንግስት ከዓመት ወደ ዓመት የሰብዓዊ መብት አፈፃፀሙን ለማሻሻል በቁርጠኝነት እያደረገ ያለውን ጥረት ሰሚ እንዳያገኝ ለማድረግ ያለመ ነው። ይኸው እኩይ ተግባር ኢትዮጵያን በተገኘው አጋጣሚ ለማፍረስ ተልዕኮ በተሰጣቸው ኃይሎች የሚከናወን መሆኑን በግልፅ ያመለክታል።

እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች የኢትዮጵያን መንግስት በአመፅ ከስልጣን ለማውረድ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ስለመሆናቸው ከግብረ አበሮቻቸው ጋር በመተባበር የላኳቸውን ወንጀለኞችና እነዚሁ ወንጀለኞች ሁከት ለመፍጠር ሲሞክሩ እጅ ከፍንጅ መያዛቸውን መጥቀስ ይበቃል። እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች ሰብዓዊ መብትን አስመልክቶ በመንግስት ላይ የሚያቀርቡትን ውንጀላ አብዝተው ሲጮኹ የሚሰሙት፣ በሰላማዊ ዜጎች ላይ የኃይል ጥቃት በመሰንዘር የሽብር ተግባር የፈፀሙ ተላላኪዎቻቸው ወንጀሉን ለመፈፀማቸው በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ክስ ተመስርቶባቸው ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ ነው። የሀገራቸውን ህግ የጣሱ ወንጀሎኞችን ትክክለኛውን የህግ አግባብ በመከተል ለፍርድ እንደሚያቀርቡ ሌሎች አገራት ሁሉ፣ ኢትዮጵያም የሀገሪቱን ህግ የጣሱ ወንጀለኞችን ለፍርድ ታቀርባለች። የሽብር ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው ፍ/ቤት የቀረቡት ተከሳሾች ላይ ከፈፀሙት የወንጀል ተግባር አንፃር በሀገሪቱ ህግ ወንጀል መሆኑና ሲረጋገጥ በህጉ መሰረት እርምጃ ይወሰዳል፤ ይህን የፍርድ ሂደትም ፍ/ቤቱ ከትክክለኛው የህግ አግባብ ውጭ የፍትህ ስርዓቱን በማዛባት የሰጠው ብይን አስመስለው ያቀርቡታል፤ ያጣጥሉታል። ይህ ብቻም አይደለም፣ ፍርድ ቤቱ በእነዚህ ወንጀሎኞች ላይ የቅጣት ውሳኔ እንደሰጠ፣ አፍታም ሳይቆይ የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት እየረገጠ ነው በማለት ሌላ ሪፖርት ያቀርባሉ። ይህ ተደጋጋሚ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የሚሰነዘረው የሀሰት ውንጀላ ደግሞ ተቃዋሚ ኃይሎችና ግብረአበሮቻቸው በጋራ የሚያቀናብሩት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው።

የኢትዮጵያ መንግስትስ በዚህ መልኩ በተደጋጋሚ በሀሰት ለሚሰነዘርበት በግልፅ የተቀነባበረ ውንጀላ እንዴት አርጎ ነው ምላሽ መስጠት የሚችለው? ይህ አስፈላጊ አይደለም፤ ምክንያቱም እነዚህ ወገኖች በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ያቀረቧቸውን ውንጀላዎች መንግስት ድርጊቱን ፈፀመም አልፈፀመም መንግስትን ከማውገዝ ወደ ኋላ የሚሉ ባለመሆናቸው ነው።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በዘር፣ ብሄር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ ፖለቲካ፣ ማኅበራዊ አመጣጥ፣ ሀብት፣ ትውልድ ወይም በሌላ ማንነት ምክንያት ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት በሕግ ፊት እኩል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ማንኛውም ዜጋ በሀገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማህበራትም ሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከህግ በላይ አይደሉም። በዚች አገር ሁሉም ሰው በህግ ፊት እኩል ከመሆኑ አኳያ አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባው ዋነኛ ጉዳይ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት አራማጅ እንደሆኑት ሌሎች የዓለማችን ሀገራት በኢትዮጵያም በህጋዊ መንገድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሰላማዊ መንገድ ተወዳድረው የመንግስት ሥልጣን የመያዝ ህገ መንግስታዊ መብት ያላቸው መሆኑ ነው። ነገር ግን ግዴታን የማያስከትል መብት እንደሌለ ሁሉ፣ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ለሚንቀሳቀስበት ሀገር ሕግ ተገዥ መሆን ይጠበቅበታል፤ ያለሕግ የበላይነት ህግ ሊከበርም ሆነ የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እውን ሊሆን አይችልምና።

እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎችም ለሀገሪቱ ሕግ ተገዥ አለመሆንን የመረጡት ያለምክንያት አይደለም። ሕዝባዊ አመኔታን ሊያስገኝላቸው የሚችልና ለሕዝብ የሚጠቅም ማናቸውንም አማራጭ ሃሳብ በማቅረብ ሕዝብን ከጎናቸው ማሰለፍ ስለማይችሉ ነው። በመሆኑም ነፃና ፍትሃዊ በሆነ የመድብለ-ፓርቲ ምርጫ ውስጥ ቢሳተፉ ሕዝቡ ይሁንታ ሰጥቷቸው ስልጣን ሊይዙ የሚችሉበት ዕድል እንደሌላቸው ያውቁታል። ለዚህም ነው በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል ማድረግ ከሚችሉበት ሀገር ሸሽተው፣ ህጋዊ ተጠያቂነት ሳያርፍባቸው የጥላቻ ፖለቲካ ቅስቀሳ ማሰራጨት በሚችሉበት እና በርካታ ዲያስፖራ በሚገኝበት ሀገር መኖርን የመረጡት።

የውጭ መንግስታት እነዚህን ፅንፈኛ የጥላቻ ፖለቲካ አቀንቃኞች በመደገፍ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ በሚያሳድሩት ጫና ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ይገባናል የሚሉትን የመንግስት ስልጣን እንደሚያገኙ አድርገው ያስባሉ። አሳዛኙ ነገር ደግሞ ከእነዚህ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል ይህን መሰረት የሌለው የተጋነነ ዲስኩራቸውን እውነት አድርገው የሚወስዱ ወገኖች ጥቂቶች አለመሆናቸው ነው፤ ለዚህም ማረጋገጫ መስጠት ካስፈለገ እነዚህ አክራሪ ኃይሎች ተስፋ ከቆረጡ ዲያስፖራ ክንፍ አባላት ከሚገኙ ደጋፊዎቻቸውና የገንዘብ ርዳታ ከሚያረጉላቸው ጭፍሮቻቸው ጋር ሆነው በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት አያያዝን አስመልክቶ አሉታዊ ዘገባ በወጣ ቁጥር በደስታ ሎቢ ሲረግጡ

መታየታቸው ነው። ከእነዚህ ደጋፊዎች መሀል ያሏቸውን የሚያምኑ ድልሎችም አይጠፉም። እነዚህ ወገኖች አንዳንድ የውጭ መንግስታት በኢህአዴግ መንግስት መቃብር ላይ ሀገር ውስጥ ገብተው ስልጣን እንዲይዙ አስፈላጊውን እገዛ እንደሚያደርጉላቸው አድርገው ሁሉ ያስባሉ። በውጭ ከሚገኙት ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል በውጭ መንግስታት እገዛና ድጋፍ ስልጣን እንይዛለን የሚለው እምነት ይበልጡኑ ጎልቶ የሚንፀባረቀው የኢህአዴግን መንግስት ሀገር በመክዳት (በማፈራረስ) ወንጀል በመክሰስ በሚታወቁት የትምክህተኛ ቡድኖች ዘንድ ነው።

እነዚህ ትምክህተኛ ቡድኖች ከአክራሪዎቹ ተቃዋሚ ኃይሎች በሁለት ነጥቦች የተለዩ ናቸው። አንደኛው መለያቸው ስልጣን ሲይዙ ሀገሪቱን በመበታተን የሚወነጅሏቸውን በሀገር ውስጥ ስልጣን የያዙ የፖለቲካ ኃይሎች ላይ ትምህርት ሰጪና የማያዳግም የቅጣት እርምጃ እንደሚወስዱ ቃል ሲገቡ ይስተዋላሉ። ሁለተኛው መለያቸው ደግሞ ይቺን አገር ለመምራት የተመረጡ፣ እውነተኛ ኢትዮጵያውያን እኛ ብቻ ነን ብለው የሚያምኑና ራሳቸውን ከሌላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ ከፍ አድርገው የሚያዩ መሆናቸው ነው። አክራሪዎቹም ሆኑ ትምክህተኞቹ ተቃዋሚ ኃይሎች ይህን አቋማቸውን ያለፍርሃት ሲደሰኩሩ ዓመታትን ቢያስቆጥሩም ከውጭ ሃይሎች ካገኙት የገንዘብ ድጋፍ በስተቀር በፖለቲካው መስክ ይህን ውጤት አስመዝግበናል ብለው ሊጠቅሱት የሚችሉት አንድም ነገር የላቸውም፤ አንድም ነገር። ከውጭ ኃይሎች ያገኙትን የገንዘብ ድጋፍም በማናቸውም መልኩ በመጠቀም በእጅጉ የተራቡትንና ሲናፍቁት የኖሩትን የመንግስት ስልጣን ይገዛልናል ብለው ያልማሉ።

የሀገሪቱ የፖለቲካ ስርዓት ማናቸውንም ዓይነት ሰላማዊ ተቃውሞ የሚፈቅድ ሆኖ ሳለ እነዚህ ተቃዋሚ ኃይሎች ሁከትና አመፅ በማነሳሳት ለውጥ ለማምጣት መምረጣቸው ትክክለኛ አማራጭ ለመሆኑ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አይችሉም። በሰላማዊ መንገድ ተቃዋሚ መሆን የሕዝቡን ይሁንታ አግኝቶ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚያስችለውን አብላጫ ድምፅ የማስገኘት/ማግኘት ዕድልንም ይፈጥራል። ህገ መንግስቱ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ምቹ መደላደል የፈጠረ ቢሆንም እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚዎች ግን ታማኝ ተቃዋሚ በመሆን ከሕዝቡ ድጋፍ እናገኛለን ብለው አይጠበቁም። እዚህ ጋ ሊሰመርበት የሚገባው ዋነኛ ነጥብ የሀገሪቱ ህገ መንግስት የመንግስት ለውጥን የሚፈቅደው በየአራት ዓመቱ በሚካሄድ ፍትሃዊ ነፃ ምርጫ ብቻ ሲሆን ይህም አብዛኛው ህዝብ

በምርጫ ይሁንታን የሰጠው ፓርቲ የመንግስት ስልጣን የሚይዝበት ስርአት ነው። በምርጫ የአብዛኛውን ህዝብ ይሁንታ ከማግኘት ውጭ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚያስችል ሌላ ምንም አይነት አቋራጭ መንገድ የለም። ችግሩ እነዚህ በውጭ ኃይሎች የሚረዱት አክራሪ ኃይሎች ለአንድ ሀገር ሰላምና መረጋጋት ብቸኛ ዋስትና የሆነውን ህገ-መንግስታዊ ስርዓት አለመቀበላቸው ነው። ለዚህም ነው ምን ጊዜም በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማምጣት ያስችላል የሚሉትን የማጭበርበር ስትራቴጂ ከመንደፍ ወደ ኋላ ብለው የማያውቁት። ለዚህም ነው የኢትዮጵያን መንግስት ከስልጣን በማውረድ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ያስችለናል ያሉትን የሀሰት ውንጀላ ለመፍበርከና ሴራ ለማቀነባበር ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚሉት።

እነዚህ በውሸት የተካኑ ሃይሎች የሚከተሉት የማጭበርበር ስትራቴጂ በዓለማችን የተጭበረበረ ገንዘብ በማተም ስራ ላይ የተሰማሩ ወንጀለኞች ከሚጠቀሙት ስልት ጋር ይመሳሰላል፤ የተጭበረበረ ገንዘብ በማተም ስራ ላይ የተሰማሩ ወንጀሎኞች የሚጠቀሙበት ዋነኛ ስልት ያተሙትን ሀሰተኛ ገንዘብ ባንክ ውስጥ በሚሰሩ ተባባሪዎቻቸው አማካይነት ባንክ ከተው በህጋዊ ገንዘብ በመለወጥ ነው። በተመሳሳይ መልኩ እነዚህ በማጭበርበር የተካኑ ተቃዋሚ ኃይሎች በኢትዮጵያ መንግስት ላይ በሀሰት የፈበረኩትን ውንጀላ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤትና ለዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ይሰጣሉ። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤትም እነዚህን በተቀነባበረ መልኩ በሁለት የተፈበረኩ ውንጀላዎችን ተቀብሎ በእውነተኛ ማስረጃ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ማረጋገጫ ከሰጠ በኋላ ይፋ ያደርጋል። ይህንንም ተከትሎ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ያላቸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ይህን ሀሰተኛና አሳፋሪ ውንጀላ አትመው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችና መንግስታት ያሰራጫሉ።

እንግዲህ በዚህ መልክ ነው በዘመናችን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን እየተከታተለ በማጋለጥ ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት መከበር ቆሜያለሁ የሚለው የሂዩማን ራይትስ ዎች የተባለው ድርጅት ከጌቶቹ የተቀበለውን የተሳሳተ መረጃ አሳምሮና ከሽኖ በማቅረብ (ለተፈፀመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት መወሰድ የሚገባውን ርምጃና ቅጣት በማከል) በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚያካሂደው።

ይኸው የኢትዮጵያ መንግስትን የሚያወግዝ ሪፖርት በሂዩማን ራይትስ ዎች ይፋ እንደተደረገ በዓለም አቀፍ ተደራሽነት ያላቸው ዋና ዋና የሚዲያ አውታሮች በሪፖርቱ የቀረበው ውንጀላ በእውነተኛ ማስረጃዎች የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን ሳያጣሩ በመረባረብ ይዘግቡታል። አስገራሚው ነገር እነዚህ የሚዲያ አውታሮች ከጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር ውጭ የሪፖርቱን ትክክለኛነት ሳያረጋግጡ በእውነት እንደተፈፀመ አድርገው ማቅረባቸው ሳይሆን እያንዳንዳቸው በሚፈልጉት መልኩ የራሳቸውን አስተያየት ጨምረው ውንጀላዎቹን አጋነው ማቅረባቸው ነው። እንግዲህ እነዚህ የሚዲያ አውታሮች በሚያቀርቡት ሀሰተኛ፣ የተጋነነና ቅጥ ያጣ ዘገባ ነው፣ የኢትዮጵያን ገፅታ የማበላሸቱ ዘመቻ የሚጠናቀቀው። በውጭ ሀገር የሚገኙት አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎችም ይህንኑ የሚዲያዎች የተንዛዛ ውሸት በአስረጂነት በመጥቀስ በገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ላይ የቅጣት ርምጃ እንዲወሰድ ያለማቋረጥ ሲጮሁ የሚሰሙት።

እነዚህ የእናት ጡት ነካሾች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሰብአዊ መብት ጥበቃ በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አድርገው በማቅረብ የሚያከሂዱት የተቀነባበረ ሴራ ተአማኒነት የሌለው ብቻ ሳይሆን የአገራችንን የሰብአዊ መብት አያያዝ ለማሻሻል ምንም የሚፈይደው አንድም ነገር የለውም። የሂዩማን ራይትስ ዎች የውግዘት ዘገባ በእውነተኛ ማስረጃ ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በምንም መልኩ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት አያያዝ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ጠቃሚ ግብ ሆኖ ያገለግላል ብሎ ማሰብ አይቻልም። በተለይ የዚሁ የውግዘት ዘገባ ዋነኛ ዓላማ የኢትዮጵያ መንግስትን ህጋዊ ተቀባይነት መሸርሸር በመሆኑ እነዚህ ወገኖችን የኢትዮጵያ መንግስት ህጋዊ ተቀባይነት የማሳጣት ድብቅ አጀንዳ ለማስፈፀም ሁነኛ አሰፈፃሚዎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ቆይቷል። ለዚህም ነው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ በውጭ ርዳታ የሚንቀሳቀሱ ሲቪክ ማህበራት ኢትዮጵያ የምትከተለው ፌዴራላዊ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ለውድቀት እንደዳረጋት አድርገው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የሚያራግቡት። በትጥቅ ትግል ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ለማፍረስ ለሚንቀሳቀሱ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች አፈቀላጤ በመሆን የነሱን ጩኸት የሚጮኹት።

ይኸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈፀሙና አለመፈፀሙን ለማጣራት ሊከተለው የሚገባውን ህጋዊ አሰራር በመጣሰ (በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የሚያወጣው የሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪፖርት የኢትዮጵያን

መንግስት ሳያነጋግር የተፃፈ መሆኑን ልብ ይሏል)። የእነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ሃይሎች ወኪል ከሆኑት የውጭ ሃይሎች ጋር እጅና ጓንት ሆነው መሥራትን የመረጡት።

አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎቹ በኢህአዴግ ላይ ለሚያካሂዱት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ውንጀላ ከጎናቸው ያሰለፉት ሂዩማን ራይትስ ዎችን ብቻ አይደለም። አልሸባብና የኤርትራ መንግስትም ዋነኛ ተድርጊቶቻቸው ተባባሪዎች ናቸው። እነዚህ ወገኖች አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ የሚያካሂዱትን የውግዘት ዘገባ የሚደግፉት ከፀረ-ኢትዮጵያ አቋም አንፃር የሂዩማን ራይትስ ዎች ከጎናቸው በመቆሙ ደስተኛ ቢሆኑ አያስገርምም፤ ምክንያቱም የኢትዮጵያ መንግስትን ከሥልጣን ለማውረድ ከማንኛውም ወገን እንዲህ ዓይነት እገዛ የግድ መሻት ስላለባቸው ነው። ለምን? በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ህጋዊ የፖለቲካ መድረክ በመጠቀም የኢህአዴግን መንግስት በአደባባይ ሊያሸንፉት እንደማይችሉ ጠንቅቀው ያውቃሉና።

እነዚህ ወገኖችም ሆነ የአክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች ፀረ-ኢትዮጵያ አቋማቸው እውን ለማድረግ ሲያስቡ ቀድመው የተረዱት አንድ ነገር አለ። ይኸው በሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የውግዘት ዘገባና ትዕዛዝ ብቻ የኢትዮጵያን መንግስት ከሌላው ዓለም ሊያገሉት እንደማይችሉ አሳምረው ማወቃቸው ነው። ለዚህም ነው እነዚህ አክራሪ ተቃዋሚ ኃይሎች ከሂዩማን ራይትስ ዎች ጋር አጋርነት የፈጠሩት፤ እነዚህ ሁለት ወገኖች የተቋቋሙበት ዓላማ ፍፁም የተለያየ ከመሆኑ አንፃር አጋርነት የፈጠሩት ከየትኛው በጋራ ከሚያስተሳስራቸው ዓላማ ተነስተው ነው ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። ግንባር የፈጠሩት የኢትዮጵያን መንግስት የማፍረስ ዓላማ ስላላቸው ነው። ሆኖም ሁለቱም ወገኖች ይህን አፍራሽ አቋም በጋራ ቢያራምዱም ይህ እንቅስቃሴያቸው በኢትዮጵያና በምዕራቡ ዓለም መካከልም ሆነ በተለይ ደግሞ ራሳቸውን በማታለል የኢትዮጵያን መንግስት ይጥልልናል ብለው ከሚያምኑት ከአሜሪካ መንግስት ጋር ያለውን መልካም ግንኙነት ሊያቋርጡት አይችሉም።

ቀደም ሲል በርካታ ኢትዮጵያውያን የሂዩማን ራይትስ ዎች በተደጋጋሚ በሚያወጣው ማቆሚያ የሌለው የውንጀላ ዘገባና በሀገር ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ ህጋዊ እገዳ የተጣለባቸው ተቃዋሚ ኃይሎች በሚያካሂዱት የስም ማጥፋት ዘመቻ ተደናግረው ነበር፤ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሂዩማን ራይትስ ዎች በኢትዮጰያ ላይ ከሚያካሂደው የጠላትነት ዘመቻ

በስተጀርባ ያለው ድብቅ አጀንዳ በምርጫ ሥልጣን ላይ የወጣውን የኢትዮጵያን መንግስት ተቀባይነት ለማሳጣት መሆኑን ያልተገነዘቡት ኢትዮጵያውያን ቁጥርም ቀላል አልነበረም። አብዛኛው ህብረተሰብ እነዚህ ወገኖች የሚያካሂዱት የሀሰት ውንጀላ መሆኑን ተረድቶ ከመደናገር የወጣው የሂዩማን ራይትስ ዎች አመራር አካላት የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ በእጃቸው እንዳለ አድርገው ቆመንለታል ብለው ለሚሰብኩት ዓላማ የቆሙ አለመሆናቸውን በግልፅ ከተረዳ በኋላ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ረገድ ምንም ብርሃን እንዳላየና ጨለማ ውስጥ እንዳለ አስመስለው የሚያወሩት። ለምን እንደሆነ ግልፅ የሆነው አሁን ነው፤ እነዚህ የአመራር አካላት የሚያወጡት ዘገባ ኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት የተከበረባት ሀገር እንድትሆን ካላቸው ፅኑ እምነትና ፍላጎት የመነጨ አለመሆኑን ሕብረተሰቡ ተረድቷል።

እነዚህ የሂዩማን ራይትስ ዎች አመራር አካላት በኢትዮጵያ ላይ የሚያወጡት የውንጅላ ዘገባ በሀሰት የተፈበረከ መሆኑን ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ጥቂት ማስረጃዎች በቀላሉ መረዳት ይቻላል። እነዚህኑ ማስረጃዎች መሰረት አድርገን በእነዚህ የአመራር አካላት መሪነት የሚፈበረኩ ሀሰተኛ ዘገባዎችን ጠልቀን ስንመረምረው በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ረገድ የኢትዮጵያ መንግስት ድክመት ከማሳየት ይልቅ የነሱን፣ የራሳቸውን ድክመቶች አጉልቶ የሚያሳይ ሆኖ ነው የምናገኘው።

እንደ አሜሪካዊው ምሁር ገለፃ ሂዩማን ራይትስ ዎች እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ላይ የሚያካሂደው ጭፍን ዘመቻ ዋነኛ ግብ የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ ተክለ ሰውነትም ሆነ አቋም አስቀያሚ መልክ መስጠት ነው። ነገር ግን  አስቀያሚነት እንደ ቁንጅና የሚወሰነው አሰቀያሚ መልክ በመስጠት ነው። ነገር ግን አስቀያሚነት እንደ ቁንጅና የሚወሰነው በተመልካቹ ዓይን ነው። ይኸው ምሁር እንደሚለው ኢትዮጵያ የሂዩማን ራይትስ ዎች የውግዘት ዘመቻ ሰለባ የሆነችው መንግስት መራሹ የልማት ፖሊሲ ስለምታራምድ ነው። ይህ ለሂዩማን ራይትስ ዎች ሥራ ማስኬያጃ የአንበሳውን ድርሻ በሚሰጡት አገራትም ሆነ ተቋማት ዓይን የሚወደድ ተግባር አይደለም፤ ሊሆንም አይችልም።

በርግጥም እነዚህ አገራትም ሆኑ ተቋማት በግንባር ቀደምትነት በቀለም አብዮት አራማጅነታቸው  የሚጠቀሱ ኒዮ ሊበራሎች ናቸው። ለዚህም ሂዩማን ራይትስ ዎች በ2002

ዓ.ም የተካሄደው አራተኛው ብሄራዊ ምርጫ የድምፅ አሰጣጥ ከመጠናቀቁ ትንሽ ቀደም ብሎ ያወጣውን መግለጫ ማስታወስ ይበቃል፤ መግለጫው ይፋ የተደረገበትን ቀንና ሰዓትም ሆነ ይዘቱን ስንመለከት የምርጫውን ሂደትም ሆነ አፈፃፀም ፍትሃዊነት ለማበላሸት ቀደም ብሎ የተዘጋጀ እንጂ የምርጫውን ሂደት አፈፃፀም በሚገባ መርምሮ የወጣ ዘገባ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህን የሂዩማን ራይትስ ዎች ድርጊትም በምርጫው የተሳተፈውን ህዝብ ምን ያህል አስቆጥቶት እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፤ ይኸው ህዝባዊ ቁጣ የኢትዮጵያን የምርጫ ሂደት ፍትሃዊነትን የማረጋገጥ ጉዳይ ከዚህ በኋላ በምንም መልኩ በሂዩማን ራይትስ ዎች ስር ሊወድቅ እንደማይገባ ያሳየ ነበር። ይህ የሂዩማን ራይትስ ዎች ዓይን ያወጣ ቅጥፈት ግልፅ ከመሆኑ በፊት የሂዩማን ራይትስ ዎች የበላይ አመራሮች ራሳቸውን በዓለማችን የሚገኙ አገራት መንግስታትና የሰብአዊ መብት አያያዝ ብቻ ሳይሆን የየአገራቱ የምርጫ አፈፃፀምና ውጤት ህጋዊ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጡት ዳኞች አርገው ነበር የሚመለከቱት።

ሂዩማን ራይትስ ዎች የኢትዮጵያን ስም ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳ ለመሆኑ በማሳያነት ሊጠቀስ የሚገባው ሌላው ነጥብ *የኢትዮጵያ መንግስት እጅግ አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ፈፅሟል* ሲል በ2002 ዓ.ም ያወጣው የቅጥፈት ሪፖርት ነው። በዚሁ ሪፖርት ላይ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የቀረቡት ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት ውንጀላዎች በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፉ አይደሉም። ይህም ድርጅቱ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ሳያስደግፍ እንዲህ ዓይነት ከባድ ውንጀላዎችን የያዘ ሪፖርት በኢትዮጵያ ላይ ለማውጣት መድፈሩ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ከፍተኛ ቅሬታ አሳድሮበት ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት የድፍረቱን መንስኤ ከሥረ-መሠረቱ ለመረዳት ወዲያውኑ በሂዩማን ራይትስ ዎች ሪፖርት የቀረበውን እያንዳንዱን ውንጀላ፣ ወንጀሉ ተፈፀመበት የተባለበት ቦታ ድረስ በመሄድ መፈፀምና አለመፈፀሙን የሚያጣራ ሀገር አቀፍ ኮሚቴ አቋቋመ።

የኢትዮጵያ መንግስት ይህን አጣሪ ኮሚቴ ሲያቋቁም ሂዩማን ራይትስ ዎች ካቀረባቸው ውንጀላዎች ጋር አያይዞ የጠቀሳቸውን የየአካባቢው የህግ አስፈፃሚ አካላትና የተለያዩ ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች እንዲያነጋግሩ ሙሉ ስልጣን በመስጠት ነበር። አጣሪ ኮሚቴውም የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞባቸዋል የተባሉትን ቡድኖች እና በህገወጥ መንገድ ተገለዋል የተባሉን ግለሰቦች ቤተሰብ አባላት ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከፍተኛ

የምርመራ ሥራ ካከናወነ በኋላ የራሱን ሪፖርት አወጣ፤ ይኸው ሪፖርት በሂዩማን ራይትስ የውንጀላ ዘገባና በተጨባጭ መሬት ላይ በተፈፀመው መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን በይፋ አጋለጠ። ይኸው የኮሚቴው ሪፖርት በሂዩማን ራይትስ ዎች የውንጀላ ዘገባና በተጨባጩ እውነታ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ ከማስቀመጡም በላይ የቀረቡት ውንጀላዎች ከእውነታው ጋር የሚጣረሱና ተዛማጅነት የሌላቸው፣ በአሉባልታና በወሬ ላይ የተመሰረቱና በሀሰት የተፈበረኩ መሆናቸውን ዘርዝሮ በማቅረብ በሂዩማን ራይትስ ዎች የቀረበው ውንጅላ በእውነታ ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን በማጋለጥ እርቃኑን አስቀረው። የኢትዮጵያ መንግስትም በሀሰት መወንጀል ለማንም እንደማይጠቅም ሂዩማን ራይትስ ዎች ለገነዘብ ይገባዋል፣ ተመሳሳይ ስህተትም እንዳይደግህም ያግዘዋል በሚል እምነት ይህንኑ የምርመራ ውጤት የያዘውን ሰነድ ህዝብ እንዲመለከተው በማለት አሰራጭቶታል፤ የሂዩማን ራይትስ ዎች ግን ያቀረበው የውንጀላ ዘገባ መሰረተ ቢስ መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ ለተሰጠው ምላሽ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ማለፍን መርጧል። ይህም ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ያለውን ንቀት በድጋሚ ያሳየበት ነበር። ሂዩማን ራይትስ ዎች ለኢትዮጵያ ያለውን ንቀት በማሳየት ረገድ በዚህ ብቻ አልተወሰነም። በቅርቡ ኢትዮጵያ “Extractive Industries Transparency International” የተባለው ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል ለመሆን ያቀረበችውን ጥያቄ ድርጅቱ ያለምንም ቅደመ ሁኔታ መቀበሉን በመቃወም ሂዩማን ራይትስ በድርጅቱ ላይ ያወጣው የውግዘት ዘገባ ለኢትዮጵያ ያለውን ንቀት በግልፅ የሚያሳይ ሌላው ማስረጃ ነው።

የሰው ልጆችን ሰብዓዊ መብት ከክፉ አደጋ የሚጠብቁ መልዓክ አድርገው ራሳቸውን የሰየሙት እነዚህ በሰብአዊ መብት ሽፋን የተቋቋሙ ድርጅቶች በተደጋጋሚ የሚያወጡት የሀሰት ዘገባ የኢትዮጵያን መንግስት የሰብዓዊ መብት አያያዝ የሚኮንንና የሚያወግዝ መሆኑን ስንመለከት እነሱ እንደሚሉት ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት መከበር ቆመው ሳይሆን ሊያሳኩት የሚፈልጉት ሌላ ስውር ዓላማ ስላላቸው ነው፤ ይህም ዓላማቸው ዓለም አቀፍ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ርዳታ እንዲያቆሙ ማድረግ ነው። ይህንኑ ዓላማቸውን እውን ለማድረግ የሂዩማን ራይትስ ዎች የበላይ ኃላፊዎች የኢትዮጵያን መንግስት የሚመራው የኢህአዴግ ፓርቲ በዜጎች ላይ የሚፈፅመው የሰብአዊ መብት ጥሰት አስከፊ ደረጃ ላይ በመድረሱ ጥብቅ ርምጃ ሊወሰድበት ይገባል ሲሉ ለኢትዮጵያ ርዳታ ለሚሰጡ ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና አገራት አቤቱታ በማቅረብ እነዚህ

ወገኖች ለኢትዮጵያ የሚሰጡትን ርዳታ እንዲያቆሙ መጠየቃቸውን መጥቀስ ይበቃል። በሂዩማን ራይትስ ዎች የተንሸዋረረ እይታ የሰብዓዊ መብትን በመጣስ የኢትዮጵያ መንግስት ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል። ኢትዮጵያ ግን ሂዩማን ራይትስ ዎች እንደሚለው ሳይሆን በሀገሪቱ ያለውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ከፍተኛ ጥረት እያደረገችና በዚህ ረገድ አበረታች ውጤት እያስመዘገበች ያለች አገር ነች።

እንደ ኢትዮጵያ መንግስት ዕይታ ሂዩማን ራይትስ ዎች በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሰብአዊ መብት አያያዝ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል እያለ አሉታዊ ዘገባ የሚያወጣበት ሌላው ምክንያት በአሜሪካና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የሁለትዮሽ (የጋራ) ምክክር መድረክ ለማፍረስ ነው። ይህ መድረክ ሁለቱ አገሮች በጋራ ጥቅሞቻቸው ዙሪያ ሃሳብ የሚለዋወጡበት ሲሆን በዚሁ መድረክ የጋራ ምክክር ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት አያያዝን የማሻሻል አስፈላጊነት ነው። በዚህ ረገድ የተሻለ ውጤት ለማምጣት በጋራ መድረኩ ከተዘረጉ የአሰራር ሥርዓቶች መካካል በኢትዮጵያ ህግ የተቀመጡትን የሰብዓዊ መብት ህጎች አፈፃፀም ለመገምገም የተዘረጋው “የክትትልና የቁጥጥር አሰራር ስልት” አንዱ ነው። ሂዩማን ራይትስ ዎች ይህ የክትትልና የቁጥጥር አሠራር ስልት መሻሻል አለበት ይላል። ከዚህ ሃሳብ በመነሳት አንድ ሰው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት አሁን በሥራ ላይ ካለው የተሻለ የሰብአዊ መብት አያያዝ የክትትልና የቁጥጥር የአሰራር ስርዓት ቢኖር እንደሚወድ አድርጎ ሊያስብ ይችላል። ይህም ብቻ አይደለም፣ አሜሪካ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር በአፈፃፀም ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለይቶ ለማወቅና ችግሮቹን ለማስወገድ የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ድጋፍ እንድታደርግ የበለጠ ያግዛታል ተብሎም ሊታሰብ ይችላል። የአንድ አገር የሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደ ተሻለ ደረጃ ከማሸጋገር የበለጠ ታላቅ ግብ አለመኖሩ የታወቀ ነው። ኢትዮጵያም እዚህ የላቀ ግብ ላይ ለመድረስ ተጨባጭ መሻሻሎችን እያሳየች ነው። ይሁን እንጂ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት እ.ኤ.አ. በ2013 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ተስፋ የሚያስቆርጥ እንደሆነ አርጎ ነው ያቀረበው። እውነተኛውን በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የሰብዓዊ መብት አያያዝ የተሳሳተ ምስል የሚሰጠው ይኸው በጥናት ላይ የተመሰረተ ነው በተባለው ዘገባ ላቀረበው ውንጀላ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው እውነተኛ የዓይን ምስክሮች

በመጠቀም ሳይሆን የሰሙትን እንዳዩ አድርገው ምስክርነት የሰጡ ሀሰተኛ የመረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ ነው።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት በዚሁ የውንጀላ ዘገባው የኢትዮጵያና የአሜሪካ የሁለትዮሽ (የጋራ) የምክክር መድረክ የኢትዮጰያ ሰብዓዊ መብት አያያዝ በማሻሻል ረገድ ያስገኘው ውጤት አጥጋቢ እንዳልሆነ ነው የገለፀው፤ የውጭ ጉዳይ መ/ቤቱ እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰው በሁለቱ አገራት የጋራ የምክክር መድረክ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ለማሻሻል የተከናወኑ ሥራዎችን የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ የተካሄደ ግምገማና ትንታኔ መሰረት በማድረግ አይደለም። ከዚህ እውነታ በመነሳት ነው የኢትዮጵያ መንግስት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት በ2013 ዓ.ም ዘገባው ማጠቃለያ ላይ የኢትዮ - አሜሪካ የሁለትዮሽ የምክክር መድረክ በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት በማሻሻል ረገድ ያስገኘው ውጤት አጥጋቢ አይደለም ሲል የሰጠው ድምዳሜ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመገንባቱ ሂደት  እያሳየች ያለውችን ለውጥና ዕድገት ሆን ብሎ ለመካዱ ሌላው ማሳያ ነው፤ በተለይም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ደንጋጌዎች ለመፈፀም የገባችውን ግዴታ ለመወጣትና በህገ-መንግስቱ የተቀመጡ የሰብዓዊ መብቶችን ህግጋት ለማስከበር ባደረገችው ያላሰለሰ ጥረት የተገኙ መልካም ውጤቶችን ሆን ብሎ ለመቀበል አለመፈለግን የሚያሳይ ነው።

ይህ ዓይነቱ የተሳሳተና የተዛባ አመለካከት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ እያሳየች ያለችውን ለውጥ መመልከት በማይፈልጉ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሃይሎች ዘንድ የሚንፀባረቅ ነው። ይህ የተዛባ አመለካከት የሚመነጨው የኢትዮጵያ መንግስት ለሰብዓዊ መብት መርሆዎች ያለው ታማኝነት ከውጭ አገራት በሚያገኘው የእርዳታ ገንዘብ መጠን ልክ ከፍና ዝቅ የሚልም ሆነ በእርዳታ ሰጪዎች ፍላጎት የሚመራ አለመሆኑን ካለመረዳት ነው፤ የኢትዮጵያ መንግስት ለሰብዓዊ መብት መርሆዎች መከበር ያለው ቁርጠኝነት የመነጨው እርዳታ ለማግኘት ካለው ፍላጎት ሳይሆን ለመርሆዎቹ መከበር ካለው ፅኑ እምነት መሆኑን የሚያውቁት ጥቂቶች ቢሆኑም በሀገሪቱ ህገመንግስት ላይ የተቀመጡትን የዴሞክራሲ መብቶች ለማስከበር የሚያደርገውን ጥረት ያህል የሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበርና የተሻለ ውጤት ለማምጣትም የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው።

ከእነዚህ በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብት አያያዝ ለማበላሸት የሚሯሯጡ ወገኖች መካከል አንዳቸውም የኢትዮጵያ መንግስት የተሻለ የሰብዓዊ መብት አያያዝ እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ምቹ መደላደል ለመፍጠር ምንም ጥረት እያደረግ ያለ መንግስት አድርገው አይመለከቱትም። ለምሳሌ የአሜሪካ መንግስት ለዚህ ምልከታው ትክክለኛነት የሚያቀርበው ምክንያት ተደጋጋሚ ድርቅና ወረርሽኝ፣ የማያቋርጥ ደም መፍሰስ እና ስር የሰደደ ድህነት ባለበት አገር ለሰብዓዊ መብት መከበር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል መደላድል መፍጠር አይቻልም የሚል ነው። ነገር ግን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ክስተቶች የነበሩት በሁሉም መልኩ የሀገሪቱን ህዝብ ኑሮና ህይወት በማሻሻል ትልቅ ለውጥ በማምጣትና አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት ስልጣን ላይ ከመውጣቱ በፊት ነው - ቅድመ 1983ቷ ኢትዮጵያ።

የኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር በሚደረግ ጥረት ብቻ የዜጎች ሰብዓዊ መብት በተሟላ መልኩ መረጋገጥ አይቻልም ብሎ ያምናል፤ እንደ ኢትዮጵያ መንግስት እምነት በተለይ የዜጎችን መሰረታዊ የህይወት ፍላጎቶች ማሟላት ባልቻሉ ደሀ አገራት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ለማስከበር የቱንም ያህል ቁርጠኝነቱ ቢኖር በዚህ ረገድ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን የዜጎችን የሕይወት ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። እንደ ኢትዮጵያ መንግስት እምነት የዜጎችን መሰረታዊ የሕይወት ፍላጎቶችን የማሟላት ጥያቄ በራሱ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች መከበር ጥያቄ ነው። በመሆኑም ለኢትዮጵያ መንግስት የዜጎችን የሕይወት ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ የማረጋገጥ ጉዳይ በዋነኛነት የዜጎችን የምግብ  ዋስትና ከማስከበር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ መሰረታዊ የተባሉትን የጤና አገልግሎቶችና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ዜጎች ከማዳረስ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው።

በሰብዓዊ መብትና በልማት መካከል ያለውን ትስስር፣ የማይነጣጠሉና የእርስ በርስ ተመጋጋቢነት እዚህ ያነሳነው አንባቢን ባነሳነው ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዳያተኩር ለማድረግ በማሰብ አይደለም፤ ይልቁኑም የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ሰጪ ተቋማትና የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ካልተስፋፉ የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር አይቻልም ባይባል እንኳን የራሱ ወሰንነቶች ይኖሩታል ከሚል መሰረታዊ እምነት የመነጨ መሆኑን ለማመላከት እንጂ። ዜጎች ለመኖረ የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማዳረስ የሚያስችል የመሰረተ ልማት አቅርቦት

ባልተስፋፋበት፣ ለአብዛኛው ዜጋ የሲቪክ ትምህርት ባልተዳረሰበት ሁኔታ በዜጎች ላይ የሚፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠርም ሆነ የአገሪቱን የሰብዓዊ መብት አያያዝ ወደተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አይቻልም። ከዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት በኢትዮጵያ በስፋት እየተከናወኑ ያሉትን የመሰረተ ልማት አውታሮች የመገንባት ሥራ ለዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር የላቀ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክቱ በግልፅ መገንዘብ ይቻላል። የሰብዓዊ መብት ተማጋች ድረጅቶች ግን ይህን ሀቅ መቀበል አይፈልጉም። (በክፍል ሁለት ይቀጥላል።)